# በአንድ የቡና ማሳ ላይ የብዝሀ ሕይወት ተጠብቆ ቡና ማምረት ይቻላል?

ቡና በተለያዩ የጥላ ዛፍ ዝሪያዎች ጥቅጥቅ ባለ የደን ሽፋን ስር ሲበቅል ለብዙ ወፎች፣ አበቦች እና ነፍሳት ተስማሚ አካባቢ ይፈጥራል። ነገር ግን አርሶ አደሩ ከፍተኛ ምርት ለማግኘት የግብርና ግብአቶችን በመጠቀምና የማሳዉን አያያዝ ማጠናከር ከፈለገ ለዕፅዋትና እንስሳት መኖሪያነት ያለው የማሳዉ ጥራት ሊቀንስ ይችላል። ይህንን በተለያዩ ግቦች መካከል ያለውን ግጭት ማለትም ብዝሀ ህይወትን መጠበቅ ወይም ማሻሻል ወይም የቡና ምርትን መጨመር አጥንተናል። በጣም ዝቅተኛ የቡና ምርት ያላቸው ጫካማ ቦታዎች ለዱር እፅዋት ከፍተኛ ዋጋ እንዳላቸው የጥናታችን ውጤት ያሳያል። ይህ ማለት የደን ቡና አያያዝን ማጠናከር የብዝሀ ህይወት መጥፋት ያስከትላል። ይሁንና ትንሽ ከፍ ያለ ምርት በሚሰጡ ቦታዎች ላይ ምርትን እና ብዝሃ ህይወትን ለመጨመር ዕድሎች ሊኖሩ የሚችሉ ይመስላል። ስለሆነም ገበሬዎች ምርትን እና ብዝሃ ህይወትን በአንድ ጊዜ የማሻሻል ዘዴዎችን እንዲሞክሩ እናበረታታለን።

### ሊጋጩ የሚችሉ ግቦች

ኢትዮጵያ ውስጥ ቡና በአጠቃላይ በአገር በቀል ዛፎች ጥላ ሥር ይበቅላል። የዛፎች መኖር በራሱ ለብዙ ሌሎች ዝሪያዎች አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ለምሳሌ፣ የዛፉን ጥላ ሽፋን ቀና ብለው ከተመለከቱት ከቅርንጫፎቹ ላይ የተንጠለጠሉ አበቦችን ማየት ይችላሉ፤ እንዲሁም ማለዳ ላይ የተለያዩ የወፎች ዘፈንና የሚያፏጩ ነፍሳቶችንና የተለያዩ እንስሳቶችን ማራኪ ድምፅ ይሰማሉ (ምስል 1)። በዚህ ምክንያት ጥላ ሥር የሚበቅሉ የቡና እርሻዎች በመልክዓ ምድሩ ውስጥ ለብዝሀ ሕይወት አስፈላጊ ቦታዎች ናቸው። ይሁን እንጂ የቡና አምራች ግን ከእንስሳት ወይም ከዕፅዋት ብዝሀ ሀብት መጠን ይልቅ ከምርቱ ገንዘብ በማግኘት ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ። የቡና እንክብካቤም በቡና አምራቾች መካከል ይለያያል። አንዳንዶቹ ቡናን ከተፈጥሮ ደን ወይም ጫካ ሲለቅሙ፣ ሌሎች ደ ግ ሞ ከቤተሰቦቻቸዉ በዉርስ ከተረከቡት የ ቡና ማሳ ቡናን በባህላዊ መንገድ ያመርታሉ፤ የተቀሩት ደግሞ በዘመናዊ ሁኔታ የግብርና ግብዓቶችን በመጠቀም እና ብዙ ጊዜያቸዉን እዚሁ ሥራ ላይ በማዋል ምርቱን ለማሳደግ ይሞክራሉ። ይህ የቡና ማሳ እንክብካቤ ልዩነት የዛፉን ሽፋን እና የጥላ ዛፎች ስብጥር ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፤ ይህ ደግሞ የብዝሀ ህይወት ስብጥር/ቅንብር ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል።



ምስል 1. በጥላ ዛፍ ስር የሚያድግ ቡና ለተለያዩ ዕፅዋትና እንስሳቶችም መኖሪያ ነው። በዛፎች፣ ግንድ አልባ ተክሎች ወይም ቅጠላ ቅጠሎች እና ብራዮፊቶች ላይ ትኩረት አድርገናል (የመጀመሪያው ረድፍ)።

## በ60 የቡና እርሻዎች ላይ ምርትና ብዝሀ ሕይወት

ጥናታችን ትኩረት ያደረገዉ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በጂማ ዞን በጌራና ጎማ ወረዳዎች ቡናን በሚያመርቱ 60 የተለያዩ እርሻዎች ላይ ነበር። በእያንዳንዱ ቡና እርሻ ውስጥ ዛፎችን፣ ቁጥቋጦዎችን፣ ግንድ አልባ እፅዋቶችን (በዛፎች ላይ ያሉትን ጨምሮ) እና ብራዮፋይቶችን (በግንድና ቅርንጫፎች ላይ የሚበቅሉ ጥቃቅን አረንጓዴ ተክሎች) አጥንተናል። ጥናቱ ከጫካ ቡና ጀምሮ እስከ ዘመናዊ የቡና አመራረት ዘዴዎች ያሉትን ያካተተ ነው። በእያንዳንዱ ጣቢያ ለሶስት አመታት በቡና ማሳ ላይ የቡና ምርታማነትን ጨምሮ ሌሎችንም መረጃዎችን ሰብስበናል።

## ምን አገኘን?

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ የዛፍ ዝሪያዎች የተገኙት ዝቅተኛ የቡና ምርት ባሉባቸው ቦታዎች ነው። ነገር ግን ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ምርት ባላቸው ቦታዎች ምርቱ እየጨመረ ሲመጣ የዛፎ ዝሪያዎች ቁጥር የማሽቆልቆል አዝማሚያ አልታየም (ምስል 2)። የቡና ምርት እየጨመረ ሲሄድ የግንድ አልባ እጽዋቶች እና የብራዮፋይት ዝሪያዎች ብዛት አልቀነሰም። ይሁን እንጂ የግንድ አልባ ዕፀዋትና የብራዮፋይቶች የዝሪያ ቅንብር በጣም ዝቅተኛ ምርት ባላቸው ቦታዎች እና ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ምርት ባላቸው መካከል ይለያያሉ።




ምስል 2. ዝቅተኛ የቡና ምርት ባለባቸው ቦታዎች የዛፍና ቁጥቋጦዎች ዝሪያ ቁጥር በጣም ከፍተኛ ነው። ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ ቦታዎች አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ዛፎችና ቁጥቋጦዎች አሏቸው።

## መደምደሚያ፣ ምክራዊ ሐሳቦች እና ያልተመለሱ ጥያቄዎች

ከጥናታችን መረዳት እንደተቻለው ዝቅተኛ የቡና ምርት ያላቸው ቦታዎች ከሌሎች ቦታዎች የተለየ ብዝሃ ህይወት ያላቸው ናቸው። ይህ ማለት የነዚህን ቦታዎች እንክብካቤ በዘመነ መልኩ ማጠናከር (ለምሳሌ የዛፍ ጥላ መቀነስ) በአካባቢዉ ያለውን የብዝሃ ሕይወት እሴት ይቀንሳል ማለት ነው። ነገር ግን፣ ከዚህ በጣም ዝቅተኛ ምርት ከምሰጡት ቦታዎች ውጪ ባሉት ማሳዎች/አከባቢዎች ከፍተኛ ምርትንና ብዝሃ ህይወትን የማጣመር እድሎች ያሉ ይመስላል (ምስል 3)።

እዚህ ላይ የብዝሃ ሕይወት እሴቶችንና የቡና አምራቾችን ገቢ እንዴት በአንድነት ማሳደግ እንደሚቻል ዕድሎችን ማሰብ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። የቡና ምርት በተሻለ የማሳ አያያዝ (ቡና መጎንደልን ጨምሮ) ሊጨምር ይችላል። ገበሬዎች ዘላቂ የምርት ስርዓትን በሚያራምዱ ድርጅቶች እዉቅና ካገኙ ምርታቸዉን በተሻለ ዋጋ በመሸጥ ገቢያቸዉ ሊጨምሩ ይችላሉ። የጥላ ዛፍ ዝሪያዎችን ቁጥር በመጨመር እና አንዳንድ የእርሻው ክፍሎች የበለጠ ጥቅጥቅ ያለ የጥላ ዛፍ ሽፋን እንዲኖራቸው በማድረግ ብዝሃ ህይወትን መጨመር ይቻላል።

የምርት መጨመር የብዝሃ ሕይወት መጨመር



ምስል 3. ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ የቡና እንክብካቤ ዘዴዎች የቡና ምርትን ለመጨመር እና ብዝሃ ህይወትን ለማሻሻል ዕድሎች ሊኖራቸዉ ይችላል። ዝቅተኛ ምርት ከሚሰጡ የጫካ ቡና ውጭ ባሉ አካባቢዎች ሁሉም ሰው ለዚሁ ጥምር ግብ እንዲተጋ ምክራችን ነዉ።


ይህ ጥናት በVR/SIDA የተደገፉ ሁለት ፕሮጄክቶች፡- “*የቡና እንክብካቤ በኢትዮጵያ የገበሬዎችን ኑሮና ብዝሃ ህይወትን ለማሳደግ*” እና “*በኢትዮጵያ አነስተኛ የቡና አምራች አካባቢዎችን ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ማላመድ*” ላይ የተመሰረት ሲሆን ጥናቱን የመሩት Kristoffer Hylander kristoffer.hylander@su.se, Ayco Tack ayco.tack@su.se, በየነ ዘውዴ beyu2009@gmail.com እና ብሩክ አያሌው biruk.ayalew2@gmail.com ናቸው ። ለበለጠ መረጃ www.su.se/deep ይመልከቱ።